# ቅዱስ አለመርካት(Holy Dissatisfaction)

ቅዱስ አለመርካት(Holy Dissatisfaction)ማለት በቀጥታ ሲተረጎም ባለንበት የቅድስና፣ከአለም የመለየት እና ከጌታ ጋር ያለን ህብረት ደረጃ ስለማያረካን የምናደርገው እየጨመረ የሚሄድ ትጋትና መሰጠት ነው፡፡በሌላ አገላለጽ ፖዘቲቭ የሆነ እየጨመረ የሚሄድ ጤናማ የሆነ መንፈሳዊ ቅናትና ፍለጋ ነው፡፡በዚህ አይነት ግስገሳ ወደ መንፈሳዊው አለም እየጠለቀ የሚሄድ ሕይወት ደግሞ ብዙ እርካታና እረፍት ይኖረዋል፡፡በመንፈሳዊ ህይወታችን ብዙ ትጋት በጨመርን ቁጥር ብዙ መንፈሳዊ በረከቶች መለቀቅ ይጀምራሉ፤የእግዚአብሄር ጸጋ እየጨመረ ስለሚመጣ ለብዙ ፍለጋ እንጠናከራለን፡፡በዚህ ሂደት ጸንተን ብንገፋ የሚገርም ኡደት(cycle of pursuit) ውስጥ እራሳችንን እናገኘዋለን፡፡በተግባር ደረጃ ቅዱስ አለመርካት ማለት አንብበን የማንጠግብበት፤የእግዚአብሄርን ቃል ሰምተን የማንረካበት፤ጸልየን በቃ የማንልበት እየጨመረ የሚሄድ የተቀጣጠለ(vibrant) ህይወት ነው፡፡መጸለይ እንጂ አለመጸለይ አንችልም፡፡ማንበብ እንጂ አለማንበብ አንችልም፡፡መስማት እንጂ አለመስማት አንችልም፡፡

እዚህ ኡደት (cycle of pursuit) ውስጥ ስለገባ ይመስለኛል ኤር 20፡7-9፣11 ላይ ባንድ በኩል(በከፊል)ኤርምያስ "አታለልከኝ"ያለው-ይህ የኔ መረዳት ነው፡፡ማለትም እራሳችን ወደ ስጋ ሀሳብ ተመልሰን ካልገታነው በስተቀር ይህ ፍለጋ፣ቅናትና ረሀብ ማብቂያ የለውም፡፡እግዚአብሄር እያታለለና እየሳበ ወደ ጠለቀ ነገር የሚከተን ህይወት ነው፡፡በነገራችን ላይ ይህንን ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ የሚደግፉ ቃሎች መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን-ቅዱስ አለመርካት የእግዚአብሄር ፈቃድ መሆኑን ያሳዩናል፡፡እስቲ አንድ ሶስት ጥቅሶችን ልጥቀስ፡-

1.ኤፌ 3፡19 «እስከ  እግዚአብሄር ፍጹም ሙላት ትሞሉ ዘንድ....»

2.ሮሜ 12፡11 «በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ»

3.ኤፌ 5፡16-20 «መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነው (በነገራችን ላይ መጠጥም ባይሆን ብዙ የሚያሰክር  ነገር አለ)

4.ሀዋ 18፡25 «አጶሎስ የዮሀንስን ጥምቀት ብቻ አውቆ በመንፈስ ሲቃጠል»

ልባችን ሙሉ በሙሉ ጌታ ላይ ሆኖ በዚህ አይነት ቅናትና ፍለጋ (passion and craving) ስንቀጥል፡-

- ጌታን በሚገባ እያወቅነውና ልባችን በመንፈሳዊ መረዳት እየተለወጠ ይመጣል
- እውነተኛ የሆነ መንፈሳዊ ደስታ እና እረፍት ወደ ህይወታችን ይመጣል(1ጴጥ 1፡7-9)
- ከዚህ የተነሳ ብዙ በሕይወታችን አላስፈላጊ የሆኑ እና መንገድ የሚዘጉ ነገሮችን እንጥላለን
- መሰጠታችን ይጨምራል
- የእግዚአብሄር መንግስት ሀሳብ ይወርሰናል

ወደ እዚህ ወደ ተባረከ ህይወት ለመግባት የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ተሰጥቶናል(1ጴጥ 1፡3)፡፡አሁን የእኛ ድርሻ ይህንን በውስጣችን የታመቀ ሀይል በሚገባ እንዲለቀቅ ማቀጣጠል ነው ፡፡ምሳሌ 26፡21 ላይ «ከሰል ፍምን እንጨት እሳትን ያበዛል»እንደሚል ብዙ ማገዶ(የእግዚአብሄር ቃል) ወደ ውስጣችን መከተት ያስፈልገናል፡፡በተገኘው ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሄርን ፊት መፈለግም ይኖርብናል፡፡ከጸሎታችን ጋር ጾም አብሮ ቢጣመር እጅግ አስደናቂ ነገሮችን እናይበታለን(ኢሳ 58)ብዬ አምናለሁ፡፡

ሀዋርያው ጳውሎስ እዚህ ቅዱስ አለመርካት ውስጥ ስለነበር ነው ፊሊ 3፡12-15 ላይ እንዲህ ብሎ የተናገረው፡-‹አሁን እንዳገኙሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ፡፡ወንድሞች ሆይ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቆጥራለሁ ነገር ግን  አንድ ነገር አደርጋለሁ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሄርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ፡፡እንግዲህ ፍጹማን የሆንን ሁላችን ይህን እናስብ....›ይህ ቃል ቅዱስ አለመርካትን የሚያመጡ ሁለት መተግበር ያለባቸውን ነገሮችን ያሳየናል፡፡እነርሱም እነዚህ ናቸው፡-

1.በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ ፡፡ያለፉ ጥፋቶች፣ውድቀቶች፣ስኬቶች እና ድሎችም ጭምር ወደ ፊት እንዳንዘረጋ ሊያደርጉን ይችላሉና ነው፡፡

2.በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፡፡በፊታችን ተዝቆ የማያልቅ ብዙ መንፈሳዊ ሚስጥርና በረከት አለ፡፡ጌታ አይናችንን ከፍቶ ያሳየን!ስለዚህ ወገናቼ ማንኛውንም በኋላችን ያለውን እየረሳን ጌታ ያሰበልንን መንፈሳዊ በረከት ለመያዝ እንዘርጋ!

## ስለዚህ አንታክትም

መታከት ማለት መሰልቸት ፣ፍላጎት ማጣት ፣ተስፋ መቁረጥ፣ሀይል ማጣት የሚሉትን ሀሳቦች ይወክላል፡፡በክርስትና ህይወታችን ሊያታክቱን የሚችሉ ነገሮች ብዙ ናቸው፡፡ለምሳሌ ለውጥ ማጣት፣የመከራ ብዛት፣ስደት፣ደጋግሞ መውደቅ፣መገፋት ወዘተ በአበይትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡የእየሱስን ሕይወት በስጋችን ተሸክመን ስለምንዞር(2 ቆሮ 4፡10) ለነዚህ ነገሮች እንጋለጣለን፤ክርስትና ዋጋ ያስከፍላልና፡፡ለምሳሌ በጌታ ከመሆኔ የተነሳ ድሮ በአለም ሳለሁ አቃቸው የነበሩ ብዙ ሰዎች አካሄዴ ስላልጣማቸው እስከወዲያኛው እርቀውኛል፡፡ይሄ በክርስትና አንድ እየከፈልኩት ያለ ዋጋ ነው፡፡እንዲህ አይነት መገፋትና የሰዎች መራቅ በህይወታችን ሲበዛ ወደ መታከት እንድናመራ ሊያደርገን ይችላል፤ከጌታ ጋር ያለን ህብረት ካልጠነከረ፡፡ካስተዋልንና ስለጌታ የምንከፍለው ዋጋ እንደሆነ ከገባን ግን እጅግ ደስተኞች ልንሆን ሁሉ እንችላለን፡፡ መታከት የሚያመጣውን ክፉ መንፈሳዊ ውጤት እንደዚህ አስቀምጬዋለሁ፡-

መታከት-------›የጸሎት ህይወት መቀዝቀዝ-----›ለዲያቢሎስ ጥቃት በቀላሉ መጋለጥ-------›መሸነፍ-----------›መውደቅ

በህይወታችን ለመታከት የሚያጋልጡን ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡እኔ አንድ ስድስቱን እጠቅሳለሁ፡-
1.ተግባር መፍታት(idlness):-ምሳ 19፡15 ላይ እንዲህ ይላል-«ተግባር መፍታት እንቅልፍ ታመጣለች፤የታካችም ነፍስ ትራባለች»ይህንን በውጤት ሂደት ባስቀምጠው እንዲህ ነው የሚሆነው፡-

ተግባር መፍታት--------›መንፈሳዊ ድንዛዜና እንቅልፍ--------›መታከት--------›መንፈሳዊ ረሀብ---------›መንፈሳዊ ሞት

2.በቂ የሆነ ጊዜ በጌታ ፊት አለማሳለፍ፡-እብ 4፡16 ላይ ወደ ጸጋ ዙፋኑ ስንመጣ ጸጋና ምህረትን እንደምንቀበል ይነግረናል፡፡ወደ ጌታ ካልቀረብን ግን ምህረትና ጸጋ ስለሚጎድለን በቀላሉ እንታከታለን
3.የእግዚአብሄርን ቃል በበቂ ሁኔታ አለመመገብ፣አለማጥናትና አለማሰላሰል መንፈሳችን ደካማ እንዲሆን ስለሚያደርገው በቀላሉ ልንታከት እንችላለን፡፡ኤፌ 3፡17 ላይ «በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ እንድትጠነከሩ...»የሚል ግሩም ቃል አለ፡፡መንፈሳችንም የሚጠነከረው መንፈስ የሆነው ቃል ወደ ውስጣችን ሲገባና ማስተዋል ሲበዛልን ነው፡፡ለዚህ ደግሞ ከቃሉ ጋር በቂ ህብረት ያስፈልገናል፡፡
4.ከመንፈስ ቅዱስ ድምጽ ይልቅ የስጋንና የነፍስን ድምጽ ስንከተል እምነታችንና ጽናታችን ስለሚሸረሸር በቀላሉ ልንታከትና ተስፋ ልንቆርጥ እንችላለን፡፡ስለዚህ ስሜቶቻችን፣ነፍሳችንና ስጋችን የሚለንን ሳይሆን መንፈስ የሆነው ቃል የሚለንን ለመሆንና ለመተግበር መጨከን አለብን፡፡ይህ ደግሞ ትልቅ ዲሲፕሊን ይፈልጋል፡፡

5.ራእይ ወይም መገለጥ ሲጠፋ ልንታክት እንችላለን፡፡ሮሜ 16፡26 ላይ እንዲህ ይላል-‹ለአህዛብ ሁሉ የታወቀው ሚስጥር እንደ ተገለጠ መጠን ሊያበረታችሁ ለሚችለው »ይህ ማለት የወንጌል እውነት በበራልንና በተገለጠልን መጠን ነው እየበረታን የምንመጣው፡፡ በተገላቢጦሽ መንፈሳዊ ራእይ፣መገለጥና መረዳት ከህይወታችን ሲጠፋ ህይወታችን በድግግሞሽ ይዋጥና ልንታክት እንችላለን፡፡

6.የአጋንንት ተጽእኖ፡-«ባላጋራችን ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ በዙሪያችሁ ይዞራል»ብሎ ሀዋርያው ጴጥሮስ አስጠንቅቆናል፡፡አንዱና ዋነኛው መንገድ ሊውጠን የሚጠቀምበት መንገድ ደግሞ መታከትን ወደ ህይወታችን በማስረጽ ነው፡፡አትችልም፣አይሳካልህም፣የት አለ ፍሬህ፣ተሰሚነት የለህም ፣እርፊህ ብትቀመጥ ይሻላል ወዘተ እያለ አእምሮአችንን በመደብደብ የጀመርነውን ስራ ሊያስጥለን ይተጋል፡፡ስለዚህ ነቅተን በሀይል መቃወም አለብን፤በቃሉ ሰይፍም መዋጋት ይኖርብናል፡፡

እንደ አዲስ ኪዳን አማኝ እንዳንታክት እግዚአብሄር በክርስቶስ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ሰጥቶናል(2ጴጥ 1፡2-3)፡፡ነገር ግን በተግባር ደረጃ መታከት ወደ እያንዳንችን ህይወት በተለያየ መንገድ ሊመጣ ይችላል በተለይ ካላስተዋልንና ካልተጠነቀቅን፡፡ስለሆነም መታከት ወደ ህይወታችን እንዳይመጣ የእግዚአብሄርን ቃል በማጥናትና በመጸለይ ከእግዚአብሄር መንፈስ ጋር በቂ ህብረት ማድረግ አለብን፡፡

2 ቆሮ 4፡16 ላይ ያለው አንቀጽ ሲነበብ «ስለዚህ አንታክትም»ብሎ ይጀምራል፡፡የዚህም ምክንያት ከላይ እንዳንታክት የሚያደርጉ ነጥቦችን በዝርዝር ጠቅሷልና ነው፡፡ምክንያቶቹም፡-

- መፈለግንም ማድረግን በውስጣችን የሚሰራ መንፈስ ስላለ አንታክትም

2ቆሮ3፡18 የምእራፉ መጨረሻ ላይ «(መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ )ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን»ይላል፡፡ይህ ማለት በውስጣችን መታከት እንዳይመጣ ይልቁንም መንፈሳዊ ለውጥና እድገት እንዲኖረን የሚያተጋን መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን አለ ማለቱ ነው፡፡ከዚህ የተነሳ የሚቀጥለው ምእራፍ 2ቆሮ 4፤1 መጀመሪያ ላይ «ስለዚህ አንታክትም»ይላል፡፡ይህ አባባል ከምእራፍ ሶስት ጋር ተያያዥነት እንዳለው ያሳየናል፡፡

- ነገር ግን የሀይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሄር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ እቃ ውስጥ ስላለን አንታክትም

ይህ መዝገብ ጎማ ተወጥሮ እንዲቆይ በከመነዳሬ ውስጥ ያለው አየር እንደሚጠቅም ሁሉ በውስጣችን ያለው መዝገብ(ባከማቸነው ልክ)ከመታከትና ተስፋ ከመቁረጥ ይጠብቀናል፡፡የዚህን የመዝገብ በውስጣችን የመኖር ጥቅም ሲገልጽ 2ቆሮ 4፡8 ላይ እንዲህ ይላል፡-«በሁሉ እንገፋለን እንጂ ተስፋ አንጨነቅም፤እናመነታለን እንጂ ተሰፋ አንቆርጥም፤እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፤እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም»ብሎ ይዘረዝረዋል፡፡ትልቁ ነገር በውስጣችን ያለውን እምቅ ሀብት መንገዘቡ ላይ ነው የኛ ሀላፊነት  ምሳ 15፡6 «በጻድቅ ሰው ቤት ብዙ ሀይል አለ»ይላልና!

- አንዱ የእምነት መንፈስ ስላለን(2ቆሮ 4፡13) አንታክትም

ምክንያቱም ኢሳ 7፡9 ላይ እንደሚናገር እምነት ጽናትን ያመጣልና ነው

- የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን እለት እለት ስለሚታደስ(2ቆሮ 4፡16)አንታክትም

ይህ ቃል በተለይ በክርስትና ህይወታችን ዋና ቁልፍ ነገር ነው፡፡መታከት እና መሰላቸት ወደ ህይወታችን እንዳይመጣ ጠበቅ ያሉ ጸሎቶች ያስፈልጉናል፡፡የምንጸልያቸው ጸሎቶች ልክ ባትሪ ሲደግም በኤሌክትሪክ ቻርጅ እንደሚደረግና እንደገና ሊሰራ እንደሚችል ሁሉ ስንጸልይ(በተለይ በመንፈስ ስንጸልይ) እንታነጻለን፤ሀይላችን ይጨምራል፤ተስፋችን ይታደሳል ብሎም እንደገና ለቀጣይ ስራዎች እንጠናከራለን፡፡ይህ ዲሲፕሊን የሚያስፈልገውና በቀጣይነት ያለማቋረጥ መተግበር ያለበት ሀላፊነታችን ነው፡፡ለዚህ ነው «እለት እለት ይታደሳል»ብሎ የሚናገረው-የእለት ተእለት ተግባር!

በክርስትና ህይወታችን መታከት ሊመጣ እንደሚችል ከላይ ባሉ አንቀጾች ላይ ጠቅሻለሁ፡፡በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ስንሆን ምን እናድርግ ለሚለው ስድስት ተግባራዊ እርምጃዎችን በመጥቀስ ጽሁፌን እጨርሳለሁ፡-

- ጠንከር ያለ የጸሎትና የጽሞና ጊዜዎችን እንያዝ(ከጾም ጋር ቢሆን የበለጠ ይመረጣል)
- ካለንበት ሁኔታ ጋር የሚሄዱ አነቃቂ መንፈሳዊ ጽሁፎችን እናንብ፤መጽሀፍ ቅዱስን በሚገባ እናንብ፣እናጥና እናሰላስል
- ከእኛ በሚሻል የክርስትና ህይወት ላይ ካሉ ባልደረቦች ጋር በመገናኘት እንመካከር እንጸልይ
- የጠላት ተጽእኖ ሊኖር ስለሚችል እራሳችንን ትሁት አድርገን ይጸለይልን
- የአጋንንትን ምሽግ ለማፍረስ በእምነት እየተቃወምን እንጸልይ
- የተቀቡ ስብከቶችንና ትምህርቶችን እንስማ

የሀይል ምንጫችን እግዚአብሄር በመሆኑ ፊቱን በመሻትና በእግሩ ስር በመሆን ስንጠባበቀውና ስንፈልገው ታማኝ ነውና ይመጣል፤ያድሰናልም፡፡ኢሳ 40፡31 ላይ«እግዚአብሄር የዘላለም አምላክ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ ነው አይደክምም አይታክትም ማስተዋሉም አይመረመርም፡፡ለደካማ ሀይልን ይሰጣል ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል፡፡ብላቴኖች ይደክማሉ ይታክቱማል ጎበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ እግዚአብሄርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ሀይላቸውን ያድሳሉ»የሚል ግሩምና ድንቅ የተስፋ ቃል አለን፡፡ይህ የተስፋ ቃል በህይወታችን እንዲሰራ መትጋት ይኖርብናል፡፡መታወቅ ያለበት ነገር

ሁላችንም ልንታክት፣ልንሰለች፣ተስፋ ልንቆርጥ እና ልንደክም እንችላለን ነገር ግን በዚህ ጊዜ ወደ ጌታ ዘወር ብለንና ወስነን በትግእስት ጸጥታና ቆይታ በጸጋው ዙፋን ፊት ጊዜን ብንወስድ እግዚአብሄር የምህረት አምላክ ነውና ያድሰናል ያበረታናል እንደገናም በክንፍ እንድንወጣ ያደርገናል፡፡ጉልበትን የሚያድስና የሚያበረታ አምላክ ከዘላለም እስከዘላለም የተባረከ ይሁን!